Jefferson Houston PK-8 IB School
1501 Cameron Street • Alexandria, Virginia 22314
(703) 706-4400   (703) 836-7923 Fax
www.acps.k12.va.us/houston/

ኦክቶበር 2021

የተከበራችሁ የጀፈርሰን-ሂውስተን ወላጆችና አሳዳጊዎች፤

እያንዳንዱ ተማሪ ውጤታማ ይሁን (ESSA) ህግ በዲሴምበር 10፣ 2015 መፅደቁ ይታወሳል። በክፍል(ሴክሽን)1112(e)(1)(A) እንደተገለፀው የታይትል I ትምህርት ቤት የሚከታተል ቤተሰብ ከሆኑ ከልጅዎ ጋር በክፍል ውስጥ ስለሚሰሩ የትምህርት ቤቱ ሰራተኞች የሙያ ብቃት እርስዎ መረጃ የመጠየቅ መብት አለዎት።

ይህን መረጃ እርስዎ የሚጠይቁ ከሆነ የትምህርት ቤት አስተዳደር ዲቪዥኑ ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ይሰጣል፤

- አስተማሪው/ዋ የስቴቱን መስፈርት ያሟላ/ች መሆኑን እና ለሚያስተምርበት/ለምታስተምረበት የክፍል ደረጃ እና የትምህርት ዓይነት የስራ ፍቃድ መስፈርት ማሟላቱን/ቱን፣
- አስተማሪው/ዋ በድንገተኛ አስገዳጅ ሁኔታ ወይም በሌላ ጊዜያዊ መልክ በተለየ ሁኔታ ምክንያት የተመደበ/ች ስለመሆኑ፣
- አስተማሪው/ዋ የሚያስተምረው እርሱ/ሷ ሰርትፍኬት ወይም ዲግሪ ባገኙበት የሙያ መስክ ስለመሆኑ።
- መለስተኛ ባለሞያ ለልጅዎ አገልግሎት የሚሰጥ/የምትሰጥ ስለመሆኑና ይህ ከሆነ ደግሞ ያለው የሙያ ደረጃው/ዋ ።

የቨርጂኒያ ትምህርት ዲፓርትሜንት እነዚህ ሁሉ ጥያቄዎች ሊመልስ የሚችል የድረገፅ (ዌብሳይት) መረጃ አዘጋጅቶል። ነገር ግን ለተወሰኑ አዲስ አስተማሪዎች መረጃው በወቅቱ ላይቀየር ይችላል። የዚህ አገልግሎት የድረገፅ አድራሻ የሚከተለው ነው፤ https://p1pe.doe.virginia.gov/tinfo/

ይህን መረጃ ለማግኘት መጠየቅ የሚፈልጉ ከሆነ እባክዎን እኔን በስልክ 703-706-4400 ወይም በኢሜል ፤ john.mccain@acps.k12.va.us. ያግኙኝ። የልጅዎ ትምህርት በተመለከተ ሌላ ጥያቄ የሚኖርዎ ከሆነ እባክዎን እኔ ከማግኘት ወደኋላ አይበሉ።

ከምስጋና ጋር፣

ዶ/ር ጆን ሚኬን (John McCain)
የትምህርት ቤቱ ርእሰ መምህር

ጀፈርሰን ሂውስተን ቅድመ መዋእለ - 8ኛ ት/ቤት

ግልባጭ፤ ናታሊ ኤም. ሚሸል (Natalie M. Mitchell)
የታይትል I ፕሮግራሞች እና የትምህርት ቤት ማሻሻያ ዳይሬክተር